# መሪ ያጣ ትግል ሐይ ባይ የለሽ አገር

ሳሙኤል ሽፈራው ከሰሜን አሜሪካ

"ወግጅልኝ ድን፣ ወግጅልኝ ቅኔ
ወንዶች ከዋሉበት እውላለሁ እኔ"
"አለቃ መርሻ ወ/ማርያም ከጣሊያን ጋር በኋላ ተዋግተው ሰማእት የሆኑ"

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለዴሞክራሲ፣ እኩልነት ተብሎ የተጀመረው ታህሳስ 1953 ግማሽ ምዕተ አመት ሊሆነው ነው። ባለፉት ሀምሳ አመታት አያሌ ተውኔቶችን አይተናል። ከተውኔቶች መሀል አንድም አስደሳች የለባቸውም ብል ማጋነን አይሆንም።

ትግሉ በነዋይ ወንድማማቾች ተጀምሮ እነሱም ያሰቡት ሳይሟላ አለፉ። ወርቅነህ ገበየሁ፣ ገርማሜ ነዋይ፣ ጀኔራል መንግስቱ ነዋይ፣ ጀኔራል ጽጌ ዲቡ ከሚዘከሩት ትቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ንጉስ ነገስቱን ተክተው ዘውድ ለመጫን የተመኙ አልነበሩም ባገሪቱ የተንሰራፋውን መሳፍንታዊ አገዛዝና የነበረውን የአርሶ አደሩን መገፋት በመቃወም ነበር። ያለፉት አምሳ የትግልና የመከራ አመታት እንደአስተማረን፤ አወ ታሪካቸው ክብርና ሞገስ አግኝቶ ላዳጊ ወጣቶች እንዲደርስ አልተደረገም። መስዋእትነት የከፈሉበት ትግልም እንዲሁ ዳር ያልደረሰ ወይስ ግቡን ያልመታ በእንጥልጥል የቀረ ነው።

አንድ አንባገነን ሄዶ ሌላ ሲተካ ሕዝብንና አገርን በአዲስ ጉልበት ሰጥ ለጥ አርጎ ለመግዛት ያለ የሌለ ሐይሉን ይጠቀማል። ከንጉሳዊው አስተዳደር በኋላ የመጡት መንግስታት አንዱ ሌላውን በማስናቅ አንዱ ከሌላውም በመማር የከፋ እንጂ የተሻለ

EthioLion.Com

ሆነው አልተገኙም። ሕዝብና አገር በነዚሁ ተከታታይ አንባገነኖች የቁልቁል ተጓዙ። ትግሉ ሲጀመር የነበረችው አገር አይነትና ቅርጽ ዛሬ የለም። እነዚያ ታጋዮች ከሙታን ቢነሱ ዳግም ሞትን እንደሚመኙ ጥርጥር የለውም። ማን ገደላት ማን ቆራረሳት፤ ማን ሕዝቡን ጨርሶ ወደመቀመቅ ላከው፣ ማንስ ነው የምድር ገነቷን ወደሲኦልነት የለወጣት ብለው መጠየቃቸው አይቀርም ነበር። አበበ አረጋይ፣ በላይ ዘለቀ፣ ታከለ ወልደሐዋርያት፣ ገረሱ ዱኪ፤ በኋላም ተስፋየ ደበሳይ፣ ጽገዬ ገ/መድሕን፣ የእምቦቅላወቹ፤ ሕሩይ ወንድማማቾች፣ ስዩም ናኦድ፣ ሳሙኤል ሽፈራው የወደቁላት አገርን ምነው ሞትን ፈራችሁ የሚለው የመጀመሪያ ይሆን ነበር። እኛ ቋሚወችስ መልሳችን ምን ሊሆን ይችል ነበር። መልሱ ብዙ፤ ሰብጥርጥርም ነው።

ሁላችንም ልንጠየቅ የሚችሉ ጥያቄወችን ለመመለስ እንዘጋጅ፤

ጥያቄ አንድ፣ ለመሆኑ የመንግስቱ ሐ/ማሪያምን መንግስት ለምን ለጥፋት እንዲበቃ አስቻልነው‹

ወታደራዊው ደርግ ወደስልጣን ሲመጣ የተደራጀ ድርጅት ስላልነበር እራሱን ጊዚያዊ አስተባባሪ ደርግ ብሎ ያለምንም ተቃውሞ፣ እንዴውም ከዳር ዳር ተሰልፎ ዘመረለት። አወ መፈክሩም "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" ነበርና ማንስ ይህን ይጠላል። ደርግ በመጀመሪያው አመት ያለፍኡትን ታጋዮች ስም አነግቶ የነሱን አላማ ዳር ለማድረስ መሆኑን ደጋግሞ ቃል ገባ። ያርበኞችን የነበላይ ዘለቀን፣ ያፈንጉስ ታከለ ወ/ሐዋርያትን የግፍ አገዳደል አወገዘ። እነሱ ለቆሙላት አገርና ሕዝብ የሚሰራ መሆኑ ከላይ የተጠቀሰው መፈክር ተደጋግሞ ተዘመረ። "እመኑኝ ከሁለት አምት ያለፈ አልቆይም የሚለው ቃሉና ጊዚያዊ ወታደራዊ" የሚሉት ለግዜውም ቢሆን

ተስፋ ሰጭ ነበሩ። ያተስፋ ግን ብዙ ሳይሄድ ህዳር ፴፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ፷ የቀድሞ መንግስት የሲቪልና ወታደራዊ ሹማምንትን በግፍ ያለፍርድ መግደሉ አዲስና የመከራ ዘመን ደውል ሆነ። ዜጎች መደረሻ አጡ። ፍርሀት ነገሰ። ጠበንጃ ተሸክሞ የገባን ሐይል ለማሶገድ ድርጅት አስፈላጊ ነበር ሆኖም ድርጅት ባለመኖሩ ቢኖርም በሕዝብ አለመታወቁ ሕዝቡም በዙሪያ ሊያሰልፈው የሚችል የራሱ የሆነ ሐይል ስላልነበረው ነበር ግራ ቀኝ ሲረግጥ የቆየው ወታደር ባዶ የሆነውን አልጋ የጨበጠው።

በኋላ ስንሰማ የተደራጁ ድርጅቶች ነበሩን ሰማን፤ ድርጅቶቹም አብዮቱን ግብታዊ አሉት። አወ በሁለቱ ቅድመአብዮት ድርጅቶች መሀል በዋነኛ ልዩነት የተመዘገበውምና ለለውጡ አጉል ፈጥኖ ደራሽ እንዲሆን፣ መሪ እንዲያጣ ጭምር ምክንያት የሆነው የአላማ ልዩነት፣ ቀድሞውን በአውሮፓ የተደራጀው መኢሶን በአላማ ደረጃ መጀመሪያ መደራጀት ቀጥሎ ወደሕዝብ ዘልቆ መግባት ማንቃት ከዚያ ማደራጀት የሚል ለተራዘመ የማንቃት የማደራጀት አላማ የስውር ዝግጅት ነበር። ይህን የተቃወሙት በግዜው የለም ከናንት ጋር ካዘገምን ዋጋ የለውም በንጉሱ ላይና በስርአቱ ለውጥ መምጣት ላይ ሕዝብ ተነሳስቷል። ይህ ማለት መጀመሪያ እናንቃ የሚለው አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑን፣ ሕዝቡ የነቃ መሆኑን ያመላከቱ አያሌ ኩነቶች አሉ የሚለው ክፍል ጋር የተፈጠረ ልዩነት ነበር። ቆሞ ላሰበ ዛሬ ይትኛው ትክክል እንደነበር መገመት ሳይሆን ፍርድ መስጠት አያስፈልግም። ታሪክ ፈርዳለችና። በጊዜው ሕሊናዊ ሁኔታ ተሟልቶ አታጋይ ነው የጠፋ የሚለው ክፍል ትክክል ነበር። “ባጭር የተቀጨው እረጅም ጉዞ” ብለው ያቀረቡት የታሪክ መጽሀፍ ዛሬም ያንን እውነታ ያልተቀበለ ያላገናዘበ መጽሀፍ ገበያ ላይ ከዋለ አመታት ተቆጥረዋል።

ወደዋናው ነገር ልመለስና፤ አነሳሴ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪ በነባሪ ሁኔታ መመስረትና ያንን በመሰሪና በበሰለ ተስማምቶ ከመፍታት ይልቅ በቂምና በቀል መነታረክ፣ ዋነኛን ችግር ወደጎን ትቶ እኔ እበልጥ እኔ ትክክል ነኝ በሚል መለያየት። በለውጥ ፈላጊው መሐል ያለው ቋሚ ችግር ነው ጉዳት አምጭም ችግር አራዛሚም ይኸው ነበር አሁንም ቀጥሏል።

አንዳንድ ሰወች በፖለቲካው መድረክ ላለፉት ፳ አመታት የቆዩትን ግለሰቦችና የፖለቲካ ሐይሎች ላለው ችግር በዋነኛነት ይኮንናሉ ይከራከራሉም። ሌሎች ደግሞ ይህ አዲስ ትውልድ እንደቀደመው ሞቅ ያለ የትግል ስሜት የሌለው ነው። በተጨማሪም በዘመነ ወያኔ ወይም ደርግ ከወደቀ ወዲህ የተመሰረቱ የፖለቲካ ሐይሎች የታጋይነት መንፈሱም ሆነ የሞራል ብቃቱ ይጎድላቸዋል። በመሆኑም አሁን ለሚታየው የተፋዘዘና የተተራመሰ ሁኔታ መፈጠር ምክንያት ናቸው ይላሉ። ሁለቱም ጉራ በየግሉ ክርክሩን እንደያዘ ሆኖ የሚጋርት ባህርይ ግን ጎልቶ ይታያል።

ለምሳሌ ምርጫ ፱፯ ግቡን እንዳይመታ ያደረጉት ሁኔታወች ከምርጫው ቀደም ባለው ጊዜ የነበሩና የተፈጠሩ፣ እነዚያም ጎልተው እየታዩ ለማረም ምንም አይነት ሙከራ አለመደረጉ። ብሎም ይህ ዘመን የፈጠረው ቂመኝነትና በቀልተኝነት ተቃዋሚውን ከአመራር እስከ ተራ ደጋፊው አንዱ በሌላው ተቃዋሚ ያካሂድ የነበረው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከመቀራረብ፣ ከመከባበርና በጠላት ላይ ከማተኮር አግዷቸዋል። ለምርጫ ፱፯ እንቅፋቱ ብዙወች እንደሚስማሙበት፤ ሕብረት (UEDF) በ፩፬ የፖለቲካ ድርጅቶች ስምምነት ሲመሰረት ትልቅ ተስፋ በሕዝብ ልቦና አሳድሮ ነበር። ባንጻሩ በወያኔ በኩል መረበሽ ታይቷል። የዶክተር ነገደን መጽሐፍ በዘር አጥፊነት

EthioLion.Com

እስከመወንጀል ነበር የተደረሰው። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ የአቶ ሐይሉ ሻውል ድርጅትና የልደቱ አያሌው ኢዴፓ/መድህን እራሳቸውን ማግለል ተወራ።

ሕብረት በተቋቋመ ብዙ ሳይቆይ ገኘው ፓርቲ ለመደራደር ፈቃደኛ መሆኑን አብስሮ በበረከት ስምኦን እና በሕብረቱ መሪወች ዶክተሮቹ መረራ/በየነ ጋር ንግግሩ ተጀመረ ይህ በዚህ እንዳለ በትቂት ቀናት ወስጥረው የነበሩ ሁለት ድርጅቶችን ይዞ የአቶ ሐይሉና ልደቱ ቡድን ቅንጅት የተባለ ስብስብ መፍጠሩን አበሰረ። አወ ከላይ እንዳልሁት የቅንጅት መፈጠርም ሆነ ከሕብረቱ መለያየት ሁሉ የሚከፋ ነገር አልነበረም። ቂምና በቀልን ይዞ መናናቅና ጥላቻን ቋጥሮ መሆኑ ግን የኋላ ኋላ እጅ የገባውን ሕዝባዊ ድል ለማስነጠቅም ሆነ፣ ከአመታት በኋላ የተገኘውን ነባሪ መልካም ሁኔታም እስከማጣት ተደረሰ። ቂምና በቀልን አዝለው፣ ከመከባበር መነናቅን አንግሰው፣ በጠላት ላይ ከመዝመት ይልቅ በሌላ ተቃዋሚ ይሁነኝ ብለው ዘምተው እራስን ጠልፈው የጣሉ የቅድመ ግንቦት ፪፯ ድርጅቶችና ታጋዮች በራሳቸው ላይ መልሶ የወረደውን የጥፋት እሳት በመንበርከክ ማረን እንጅ አይደግመንም ብሎና ፈርሞ ከእስር መለቀቅ ነበር ያገኙት ትርፍ።

ልደቱ አያሌውን አምኖ የተሰለፈው ሕዝብም ሆነ የድርጅት አባልና ደጋፊ ተከታዩስ ምን አጋጠመው፧ ያየነው ያጭር ጊዜ ትውስታ ነው። ልደቱ ሕዝብን ክዶ ገሐድ ወጦ ሰልፉን ያሳመረውና ማንነቱን ያጋለጠው የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስቴር በምርጫ ማግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውም ሕገመንግስትና ገለልተና ፍርድ ቤት አለኝ ባለበት ሲያውጅ። ብሎም ተስፋ በቆረጠና በተበሳጨ አንደበት ድሉ የኛ ነው ብሎ እራሱ ለፈጠረው ቦርድ እንኳን ጊዜ ሳይሰጥ ማወጁ ባንጻሩ ከተቃዋሚው ጎራ በተለየም አገር ቤት ነን ካሉት አንድም መተንፈስ አለመቻል የተምታታበት የፖለቲካ

ጉዞ መጀመር፣ ሐላፊነትንም ሆነ የመሪነትን ቦታ መሸሽ ሁሉ አሳፋሪ ወራዳም ሁኔታ ነበር።።

ከምርጫው ማግስት እንደአንበሳ ያገሱት የተቃዋሚ መሪወች ሁሉ ድመት ሁነው ታዩ። የመጀመሪያ የትግሉ ሰለባ የሆኑት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪወች የሕዝብ ድምጽ ይከበር ብለው በወጡበት ቀን እነሱ ግብ ግብ ላይ እያሉ አቶ ሐይሉ ሻውልና አብረዋቸው የነበሩ መሪወች ይን ሰላማዊ ሰልፍ አናውቅም እኛ አያገባንም ብለውት አረፉ። በመጨረሽአም በመስከረም ወር ሊደረግ የታሰበውን ጠቅላላ ሰላማዊ የስራ ማቆምና የሙት ከተማ የመፍጠሩን የጋራ ስምምነት እራሳቸው በመረጧቸው ሁለት መሪወች አመከኑት። ትናንት የተሰሩ ጥፋቶችን ከቆጠርን በደርዘን ነው ይቆጥላል ለሚማር እንጅ ከስህተት ላይ ስህተት ለሚደረድርና ትክክል ነኝ ብሎ ለሚያስብ ምን ፋይዳ አለው።

ዛሬስ ምንላይ ነን፡

አሳዛኙ የኢትዮጵያ ፓለቲካ ቀጥሏል፣ ሕዝቡም "መኖር ከተባለ መቃብር ይሞቃል ይባል አይደል"፤ ይኖራል። መቸም የምድር ሐይሎች ፈርደው የዚህችን አገር የመጨረሻ ጥፋት ቢመኙላትም ያምላክ ፈቃድ ነውና ቀጥላለች። ፩፰፰፰ የቄሳሩና ፩፱፪፰ የሞሶሎኒ ዘመቻ ለትቂት አመለጠች። ክብርና ምስጋና፣ ለዘላለም ለነዚያ ግፏን ይሁንና ምንም እንኳን ታግለው ባተረፏት አገር በልጅገውና ተደስተው ባይኖሩባትም (አንች ምድር ዳግም ወንድ አይብቀልብሽ) ያለውን ያባኮስትርን በስቅላቱ ቀን የተናገራትን ይዘክሯል። አገራችንን ከውርደት ስሟም ከመጥፋት አድነዋል።



EthioLion.Com

አንድ ወዳጀ በመልካም በክፉ የምገናኘው በተገናኘን ቁጥር አበሳጭቶኝ እንለያያለን። ሁሌ የሚያስበው ከኔ በተቃራኒው ነው። አሁን ልደቱ ከሀዲ ነው ስል አይ ለምን ስለልደቱ ታስባለህ ይለኛል። ወያኔ መወገድ አለበት ስለው አዎ ግን ማን ያስወግደው፡ ተቃዋሚወች ናቸዋ። የትኛው ተቃዋሚ፣ እንደአንተ በውጭ አገር የሚኖረውን ሁሉ ተቃዋሚ ነው ልትል ነው፣ ነው ኢፒፒፍ፣ ወይስ ማን፣ ይለኛል ጭውውታችን በእንዲህ ባለ እኔን የምመልሰው አሳጥቶ እንጨርሰዋለን። አሁን ከሆነ እኔም ያው በማነኛውም የቤተሰብ ግንኙነት መገናኘታችን አይቀርምና ከሱ ጋር ፖለቲካ ለመግጠም ፍላጎቴም ስሜቴም አይደለም ግን ይሁነኝ ብሎ ያነሳብኛል በኔ ቁጣ ያልቃል። ታዲያ የመጨረሻ ቃሌ ወያኔን ስለምትደግፍ ነው እለዋለሁ። ምኔ ወያኔ ይመስላል የልቅ ማፈሪያ ንግግርህን አቁም ይላል።

በውነት የሚለው ሁሉ እውነት ሆኖ አገኘዋለሁ። በውነትም ምን ተቃዋሚ አለ፣ ለውጥ ለማምጣት ካልተነሳሳ። ለመሞት ለመሰዋት ካልተዘጋጀ ምኑን ትግልና ታጋይ ተሆነ። አንድ የአቶ በልጅግ አሊ መጣጥፍ ሁል ጊዜ ይታወሰኛል። ለማስታወስ ምክንያት የሚሆነኝ ፓልቶክ የሚባል የውጊያ ቀጠና ስገባ ነው። በዚያ የውጊያ ቦታ የሚገባ ሰው መጀመሪያ ከሚያገኛቸው አዋጊወች አንዱ ሸጋው ይባላል። ይህ ታጋይ መልኩን ወይም አድራሻውን ወይንም ያለበትን አገር እንኳን የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ላለፉት ፲ አመታት ወያኔን በመታገል የደከመ መሆኑን በምሬት ይናገራል። የመጀመሪያ ሰውን ሲገኛኝ እንኳን ደህና መጣህ አይደለም። አንተ ወያኔ አውቅሀለሁ በማለት ነው። ከጊዜ በኋላ በአካል ባያውቅም ደጋግሞ ስለአየህ ያውም የፓልቶክ ስምን ማለት ነው። ለማንም አያስነካህም (በቀይ ምልክት አትታሰርም)። እከሌ ከኛ ጋር ወያኔን በመታገል መከራውን ሲያይ የኖረ ነው ይላል።

EthioLion.Com

የቤልጅግ አሊ መጣጥፍ የሚታወሰኝ ሰአታት አልፈው አንድም ስራ ሳይሰራ ሰው ሁሉ (የእውነተኛ) ሰው፤ እጁን እያወጣ እያንዳንዱ ፳ ወይም ከዚያ በላይ ሲያወራ ይውላል። ደግሞ ደጋግሞ ወያኔን መርገም ነው። ገራሚው አንድ ክፍል ወያኔን በመርገም ሲያጓራ የዋለ ሌላ ክፍል ሄዶ የወያኔ ዝንባክሌ ካላቸው ጋር ስለልማት እና ሰለሰላም ሲያወራ ማዳመጥ የተለመደ ነው። ዲንቁም ትግል። ዛሬ ትግል የሚባለው ይህ ነው። በውጭ ያለው እንዲሁ በዚያች ጠባብ መስኮት ስለትግል ስልት ሰለወያኔ ጠላትነት ሲለፈልፍ መዋል ነው። ሰሞኑን የተያዘው ምርጫን ቦይኮት አናድርግ ነው። ባልከፋ ሐሳቡ ትክክም ነው ግን መቸ ከጠባቧ የኮምፒውተር መስኮት አልፎ፣ ወይስ ማን ማነን በምን መልክ ሊነግር ይችላል፣

ሌላ ቀርቶ ለተቸገሩ ወገኖች ገንዘብ ለማዋጣት እንኳን ስንት ፈተና አለው፣ እውነትም የድብርት ፍቱን መድሐኒት።

አስብ አስብና ይህ በኛ አገር ብቻ ነው ወይስ በሁሉም አገሮች የተከሰተ ችግር ይሆን እላለሁ። ግና መቼ እንደኛ አገር በራስ ወግኑ በባርነት የሚማቅቅ ሕዝብ አለና። ሕዝብማ ግፉ፣ ጠኔው፣ በዋለበት ጎዳናና ድልድይ ስር ማደሩ ሞልቶ ተርፎበታል። ጭቆና በደሉን በቃኝ ብሎ ከተነሳሳ አራት ድፍን አስርት አመታትን አስቆጠሯል። ከአለፋት ሁሉ የባሰ ዘረኛ ተንፈራጦ በማን አህሎኝ መግዛት ከጀመረም ይኸው ሀያ ሊሞላ አንድ ፈሪ ነው። የሕዝብን በቃኝ አልገዛም ባይነት ደግሞ ደጋግሞ ካሳየን እረጅም ቢሆንም አደራጅቶ የሚያታግል ጎበዝ መጥፋቱ ግን መከራን አልዝሞታል። ታዲያ ምን መደረግ አለበት፧

እስኪ ሁላችንም ስለተቃዋሚው እናውራ። ምክንያቱም ወያኔ የለየለት የሕዝብ ጠላትነቱ የታወቀ በተለይ ከምርጫ ፩፱፱፯ በኋላ ከዛላንበሳ እስከ ሞያሌ አንድም ደጋፊ የሌለው ከሆድ አደሮችና መሰል ጠባቦች በስተቀር ማለት ነው። መሆኑ እየታወቀ የተደራጁ ሐይሎች ግን ይህን ሕዝብ አሰልፈው ሊያሶግዱበት የሚያስችል መላው የጎደላቸው መሆኑ ያገርን መከራ ለማረዘም የወያኔ ደባሎች ናቸው ብል ስህተት አይሆንብኝም።

እኛ ስናውቀው ትግልና ታጋይ ከመስዋእትነት ተለያይተው አያውቁም። መሞት ላገር ነጻነት። መሞት ለእኩልነት። መሞት ለዴሞክራሲ ሲባል ያለ የነበረ የሚኖር ነው። የሞገስ አስገዶምና ያብርሐም ደቦጭም ሞት እኮ ለነጻነት የተከፈለ ታላቅ ዋጋ ነው። የደጃች ታከለም እንዲሁ። ልክ የዛሬ ፫፬ አመት የቀይሽብር አፍላ ወር ነበር። በዚያ ፍጅት ስንት ታጋዮችን አጣን። ሲወድቁ ፈርተው ተንቀጥቅጠው አልነበረም። አንዳያት ቅድም አያታቸው ፎክረው፣ ፍጹም ነው እምነቴ ብለው ነበር። ። መጋቢት በ፩፱፰፱ ባንድ ቀን ጀበር ያጣናቸው ተስፋየ ደበሳይ፣ ግርማቸው ለማ፣ ዮሐንስ ብርሀኔ፣ ሞትን በጸጋ ነው የተቀበሉት። አገር ጥለው አልፈረጠጡም የጀግና ሞት ሞቱ። ለአገር፣ ለወገን፣ ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲ ከባድ ዋጋ ከፈሉ። ሁልጊዜ ይዘከራሉ። ያን ያየን ዛሬ ታጋይ ነን የሚሉን ፈርጣጮች ናቸው ብንል ለምን እንሰደባለን። ምርጭን እየጠበቁ ያውም ጠላት ዶልቶና አስቦ ያዘጋጀውን ምርጫ እየጠበቁ የሚውገረገሩትን ምን እንበላቸው፣ ወይንስ ካመት አመት በመራብ አገሮች ኑሮ አድርገው ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉቱ የኔ ብጤወች ታጋይ ነን ባዮችን ምን እንበላቸው። ጓደኛየ ደግሞ ደጋግሞ የናንተ ታጋይነት ብስል ከቀዝቃዛ እያማረጣችሁ ታጋይ ትሉናላችሁ ይላል። ታዲያ እኔ መልስ የለኝም። ወዳጀ ሆነም ቀረ ከናንተ ምርጫ ጠብቀው ብቅ የሚሉት መራራና፣ በየነ ተሻሉ ይለኛል። ለሕዝብ ሀሰት አያሳዩትም።

ማንነታቸውን ሁሉም ግጥም አርጎ ያውቃል። ያስቸገሩ። መለኪያ ይዘው የትጥቅ ትግል ከተቃወማችሁ ውግዝ ከማሪዮስ ባዮች ናቸው።

እነዚህ የውሸት ታጋዮችና መሪወች በሌላው አቃቂር ሲያወጡ የውሸት ባታሊዮን ሲደረድሩ ከግራ ቀኝ ተቃዋሚውን ሲያብጠለጥሉ የሚገኙት ናቸው ችግር ላይ ያስቀመጡን። ሌላ ቀርቶ አቅም አውቀው ለመተባበር ለመመካከር ፍላጎቱም የሌላቸው ባተሌ እየሆኑብን ነው። ለምን አትታገሉም ሲባሉ የሚያታግል ሁኔታ አገር ውስጥ የለም ይሉናል። ተመልከቱ፣ ትግል ዛሬ በሁኔታ መመቻቸት ሆኗል። የደቡብ አፍሪካ፣ የችሌ፣ የፊሊፒን ሕዝቦች ትግል መራር ነበር። ታጋዩ ሁኔታወችን በደሙ ቀየረ። አንባ ገነኖችን አባረረ፣ አንበረከከ። እራሳቸውን በአደባባይ በእሳት ያጋዩ ታጋዮች ዛሬ በኢትዮጵያ ታጋይ ነን ባይ አይንና ግንዛቤ ሞኞች ሳይባሉ ይቀራሉ።

ጋይም አዲስ አበባ ከወያኔ አጋዚ ጋር ተታኩሶ ሲወድቅም ሞኝነት ያሉ የሚጠፉ አይመስለኝም። ለነገሩ እሱ ወደዚያ ሲያቀና አንዳንዶች ጓዝ ጠቅለው ይቅናሕ ብለውት አልነበር ወደምእራብ የተጓዙት። ዛሬ እሱ ባመነበት ተሰዋ እነሱ በየፈረንጁ አገር የ fulltime ሰራተኛና part-time ፖለቲከኞች ናቸው። ሁላችንን ያጠቃልላል። ያሁን ጊዜ ፖለቲከኛ የራሱን ምቾት ጠብቆ የሚንቀሳቀስ ነው። ተጨባጭ ሁኔታው ለትግል ያመቻል አያመችም ይላል። ታጋይ ነኝ ይልና ሞትን ይፈራል። ዋያኔ ክፉ ነው ይገለናል ብሎ ይሰጋል። ቀን ቀን ስራ ያለው ስራው አለያም አደራ የተባለ ይመስል ሲባክን ውሎ ማታ ከትንሿ መስኮት (computer)ፊት ሲዋጋና ሲያዋጋ ያመሻል። ወዶ አይደለም ሽጋው ድፍን ፲ አመት ወያኔ ስንዋጋ የኖርን የሚለው (ፓልቶክ ወድቦ ማለት ነው)የአሁኑ አርበኛ፣ ታጋይ፣ አገር ወዳድ ብቻ

EthioLion.Com

የምትፈልጉትን ስም በሉት፣ አገር ከጠባብ አሸባሪው የታጠቀ ሀይል ነጻ የሚያወጣ በአዲሱ የመታገያ ስልት ጫካና ዱሩን እዚያ አድርጎ ነው።

አንዳንዶች ድፍን አምስት አመት የትግል ስልትን በተመለከተ በሚደረግ የዚሁ የትንሿ መስኮት ክርክር አዱን ፈሪ ሌላውን ጀግና አርገው ሲሾሙና ሲሽሩ ይውላሉ።

በእውነትም ቤልጅግ አሊ የተባለ ወንድሜ ፓልቶክን የዘመኑ ፍቱን የድብርት መድሀኒት እንዳለው፣ ይህ ባይኖረ ስንት ሰው አብዶ ጨርቁን ጥሎ በሄደ ነበር።

ሰው እንስሳ ነው። ግን የሰለጠነ የሚያስብ፣ ክፉ ከደግ ለይቶ የሚበጀውን የሚቀበል ወይም የማይጠቅመውን የሚያስወግድ ነው። ከእንስሳ የሚለየው ይህ ብቻ ሳይሆን ወገን ከባእድ፣ ጠላት ከወዳጅም መለየቱ ሌላው የሰውነት ባሕርይ ከእንሣው መለየቱ ነው። ማንም ማንን በሰውነት በሐይል አያስገድደውም ይህ እንኳን እኛ ሰወችን እንስሶችም ግፍን፣ በደልን፣ መገፋትን ይሁንብኝ ብለው አይቀበሉትም። ታዲያ እንዴት ነው እኛ ኢትዮጵያውያን ከምሞት ተረግጬ መሰንበት የሚለውን በሰው ባህርይ ያልተለመደ አስተሳሰብ መቀበል ተቻለን። አንድ ሁላችንም ያላወቅነው ነገር አለ ተፈጥሯል። ያንን ጠላታችን አበጥሮ አውቆ ተጠቅሞበታል። አሁንም እየተጠቀመበት ነው። ያያላወቅነው ነገር በሕዝቡ መካከል እንዳልሆነ ደግሞ ከምርጫ ፲፱፻፺፯ በኋላ አበጥረን አውቀናል። ችግሩ አሁንም ቢፈተሽ ተቃዋሚ ነን በሚሉ የፖለቲካ ሐይሎችና መሪወች መካከል ነው ያለው። ትናንት ሕዝቡ “ወይ ተባበሩ አለያም ተሰባበሩ” በሚል ግፊት የተቃዋሚ ሐይሎች አንድ አንኳን መሆን ባይችሉ ሕብረትና ቅንጅት በመሆን ጠላትን እንዳርበደበዱት አይተናል። ዛሬስ፣ ተቃዋሚ ነን በሚሉ ድርጅቶችና መሪወች ተስፋውን ቆርጧል። ዛሬ ለሕዝባዊው ትግል እንቅፋቶች ስርአቱ ብቻ ሳይሆን

የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪወች ለመሆናቸው አገር ያወቀው ጸሀይ የሞቀው ጉዳይ ነው። አሮጌውን የዘውድ አገዛዝና አንባገነኑን መንግስቱን እዳስወገደ ሁሉ። ወያኔና አንዳንድ ተቃዋሚና መሪነን ባዮች ያልተናነሰ በደል በድለዋል። የሕዝቡ ጠላት ዘረኛው ወያኔ ያለአንዳች ችግር ግዛቱን፣ ጭቆናውን፣ አገር መሸንሸኑንና መስጠቱን ያላንዳች ስጋት እንዲቀጥል አባሪ ተባባሪ ሆነዋል። ትናንት ወይ አብሩ አለበለዚያ ተሰባበሩ ያለው ሕዝብ ዛሬ ከወያኔ ጋር ድራሻችሁ ይጥፉ እንደሚል ጥርጥር የለውም።

የነዚህ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶች ስራና ተግባር እርስ በእርስ መሰዳደብ ነው። በወያኔ ላይ አንድ ጠጠር ለመወርወር የተዘጋጀ ቢኖር ግፍ የበዛበቱ ሕዝብ ዛሬ ባንድ ጀንበር ሆብሎ በተቀበለው ለዚያም ነው ቀን በጸሀይ ሌት በጨረቃ ፈልጎ አፈላልጎ ላመል የተቃዋሚ እውነተኛ ባሕርይ የተላበሰ ማግኘት ያልቻለው።
አወ ነን ለማለት በማይታይ በማይዳሰስ ሕዋ (cyber) በሚሉት ጉም ገብተው ሲዳክሩ የሚውሉት የተጠረቃቀሙ ፈሪወች ናቸው። ተቃዋሚ ግን ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ሸጋው "አስር አመት ሙሉ መከራችንን ስናይ" በፖልተክ እንዳለው ማለት ነው። አሁን ጊዜ ታጋይ ነን ባዮችም ሆኑ ትግሉ አንድም አምስት አመት እየጠበቁ ምርጫ ቦርድን መዝግበኝ አልመዘግብም በሚል ግብግብ ፍርድ ቤት የሚመላለሱ ናቸው ግፋ ቢል በተዘጋጀላቸው "ፓርላማ" ድንቄም። ግብተው አንድ ሁለት ቃል ተቃውሞ መሰል የወረውራሉ። ወያኔ ብልጥ ነው ያችን በሚቆጣጠረው የቴሌቪዥን መስኮት ብቅ አርጎ ያሳያታል። ምክንያቱ ግልጽ ነው ፈረንጅም የሚፈልገው ይህን በመሆኑ በፓርላማ ያሉ ተቃዋሚወች ይህን ፖሊሲ ተቃወሙ ይላል። ይህ የምሬት ቃሌ ነው። ማንም ከደሙ ንጹ አይደለም። አገራችን ዛሬ እንደ ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ ብልጥና ሆደሰፊ መሪ ትፈልጋለች። ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣት ከታሰበ እዳው ገብስ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች የነገን ለነገ ትተው ዛሬን

EthioLion.Com

በልበ ሰፊነትና በልበሙሉነት የተባበሩ፣ ይተቃቀፋ። ጠላት አንድ ነው። እሱም (ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ) ለሆድ፣ ለስልጣን ሲል ከወያኔ ጀርባ የቆመው ባንድ ቀን እንደጉም በኖ ይጠፋል።

ወይ ተባበሩና ታገሉ አለያ ከወያኔ ጋር ተደበሉና ጥፋ

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ሳሙኤል ሽፈራው ከሰሜን አሜሪካ

EthioLion.Com